ክብር | ፍትህ | እንኳን በደህና መጡ | እርምጃ

# ፍትሓዊ እንቅስቃሴ የኢሚግሬሽን ማሻሻያ ቻርተር

FIRM

ፍትሃዊ የኢሚግሬሽን ማሻሻያ ንቅናቄ (FIRM) የህብረተሰባችን እውነታ ሊያንፀባርቁ የሚችሉ በተለይ ስደተኛን የሚመለከት ፖሊሲዎች በማካተት ፣ ዲሞክራሲያዊ እሴቶች ፣ በማስተባበር ሰብአዊ ጥሪ ያደርጋል። በተጨማሪም፡ የብሪታንያ ለሁሉም ሰው ክብር እና ፍትህ መቆም የሚለውን ታሪካዊ መርህ እምትከተል ኣገር መሆንዋን ለማስታወስም ጭምር እንዲረዳ ታስቦ የተሰራ ነው።

ቻርተሩ፡ ኣስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ከስደተኞቹ ጋር ፡ ማለት፡
ከቤተሰቦቻቸው
እና ከጓደኞቻቸው ፣ የስደትኛ የዘመቻ ቡድኖች ፣ ፖለቲከኞች ፣ ጋዜጠኞች ፣ የጉዳዩ ሠራተኞች ፣ በጎ ፈቃደኞች እና በብሪታንያ ጨካኝ የስደትኛ ፖሊሲዎች ጉዳት የደረስባቸውና፡ ኣሁንም በቀጣይ የሚበደሉ ያሉትን ሁሉ በማስተባበርና በማቀናጀት፡ የተለያዩ ሌሎች ደጋፊዎቻቸው ጭምር ያካተተ ረዘም ያሉ የብዙ ውይይቶች ሂደት ውጤት ነው።

በእነዚህ ውይይቶች የተባበረ ጥረት አማካይነት ለውጥ እንደሚያስፈልግና፣ እንዲሁም እነዚህን ለውጦች በትክክል እንዴት ማከናወን እንደሚቻል እሚያስተባብር፡ የተቀናጀ የንቅናቄ ንድፍ አውጪ ድረጅት መኖር እንዳለበት በማመን ነው።

የስደተኛ ማህበረሰቦች፡ የማህበራዊ ፍትህ ዘመቻዎች ፣ እና ተራማጅ ድርጅቶች ኣንድላይ ሆነው እነዚህን የቻርተሩ ዋና መሰረታዊ ፍላጎቶች እውን ለማድረግ የሚቀጥለው ጥያቄዎችን ያቀርባሉ ።

**Sign the FIRM Charter**

firmcharter.org.uk info@firmcharter.org.uk @FIRMCharter

Sign the FIRM Charter

# 1. ክብር እንፈልጋለን (እንጠይቃን)

- በጥላቻ የተካኑ የአከባቢ (Hostile Environment) ፖሊሲዎችና ልምዶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ፡ እንጠይቃለን፡
- ጥገኞች መበታተን እና የመበደል ፖሊሲ እንዲቆም እንጠይቃለን፡
- እኩል ተደራሽነት ለሁሉም በሚል መርህ የተመሰረተ ነጻ የጤና አገልግሎት እና እንዲሁም የብሔራዊ ጤና ኣገልግሎት (NHS) የውሂብ መጋሪያ ልምዶች (data sharing practices) እንዲቆም እንጠይቃለን፡
- የትምህርት ተደራሽነት ፣ የደህንነትና ፡ ስራ የማግኘት መብት፡ ለሁሉም ስደተኞች እና ጥገኝነት ለሚሹ፡ ሙሉና እኩል መብት እንዲሰጥ እንጠይቃለን፡
- የኢሚግሬሽን በስደተኞች ላይ ኣስገዳጅ ስራ አፈፃፀም (immigration enforcement) ማለት ፣ ሳያስታውቁ መኖርያ ቤት መፈተሽ ፣ ማሰር እና ካኣገር ማባረር ኣሁንኑ እንዲቆም እንጠይቃለን፡
- ለሁሉም ሰነድ አልባ እና በሰነድ ያልተመዘገቡ (undocumented and under- documented) ስደተኞች በእኩል ደረጃ እና ተደራሽ በሆነ የቁጥጥር ፕሮግራም አማካይነት በዩኬ (UK) ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በእኩልነት እንድታዩ እንጠይቃለን፡
- ሁሉም የባርነት ዓይነቶች እና ህጋዊ ያልሆነ የሰዎች ዝውውር እንዲቆምና የባለሙያ ድርጅቶች የውሳኔ ሃሳቦችን ተግባራዊ እንዲደረግ ፡ እንደዚሁም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲከበር እንጠይቃለን፡
- ጠንከር ያለ ሰራተኞችን የሚከላከሉ ህጎችን ትግበራ እና ያልተመጣጠነ የሁለት-ደረጃ (two-tier) ስደተኞችን የሚጎዳ የቅጥር ስርዓት እንዲያበቃ እንጠይቃለን፡
- አሠሪውን የመቀየር መብትን ጨምሮ የቤት ሰራተኞች መብቶች እንዲ መለሱ እንጠይቃለን ፣
- ፈጣንና ያለብዙ ወጪ የስደተኛ ጉዳይ እሚታይበት መንገድ እንዲ መረጥና \ የበለጠ አካታች የቤተሰብ ውህደት መስመሮችን እንዲፈለግ እና የትዳር ጓደኛ የገቢ ቪዛ ገደቦች ወዲያውኑ እንዲቆም እንጠይቃለን፡
- የልደት-መብት ዜግነት (birth-right citizenship) እንደገና እንዲቋቋም እንጠይቃለን፡
- ካአንዳንድ ቪዛዎች ጋር የተያይዘ የገንዘብ እርዳታ እገዳ እንዲቆም እንጠይቃለን፡
- ለሁሉም አውሮፓውያን ዜጎች ሙሉ እና እኩል መብቶችን እና የነፃ መንቀሳቀስ መርሆዎች መስፋፋት እንጠይቃለን፡
- የክህደት ባህል (culture of disbelief) እና ሁሉም ዓይነቶች ማለት በዘር ፣ በፆታ ፣ በሃይማኖት፣ በጾታዝንባሌ ፣ የማኅበራዊ ቡድን አባልነት ፣ የስደት ሁኔታ (migration status)፡ በትውልድ አገር፡ ኣድልዎ እንዲቆሙ እንጠይቃለን፡

FIRM

# 2. ፍትህን እንፈልጋለን (እንጠይቃለን)

**የሕግ ፍትህ፡**

- ስደትኞች ዋስትና ያለው ነፃ እና ጥራት ያለው የህግ ውክልናና ምክር እንዲያገኙ እንጠይቃለን፤
- ዋስትና ያለው የይግባኝ የማግኘት መብት እና ከሀገር ውጭ ሆኖ ይግባኝ በል ማለት እንዲቆም እንጠይቃለን፤
- በመንግስት ተቋሞች ውስጥ ገለልተኛ የሆነ የፍትህ ምርመራ እንዲደረግና የሚመለከታቸው የመንግስት መምሪያዎች የመዋቅር እና የፖሊሲ ውድቀቶች እንዲታውቅ። ከኢሚግሬሽን የስራ ቦታ ጉዳዮች ጋር ኣያይዞ፡ በተለይም የሆምኦፊስ (Home Office) የዘረኝነት ፖሊሲ እንዲ ወገድ እንጠይቃለን ፣
- በጥላቻ ኣካባቢ (Hostile Environment) ፖሊሲዎች ለተጎዱ ስደተኞች ሁሉ ካሳ እንጠይቃለን፤
- ለሰላማዊ የሰው ልጅ ካኣገር ወደ ኣገር እንዳይተላለፍ የተደረጉ እንቅፋቶች እንዲወገዱ እንጠይቃለን፤
- የስደተኞች ሁኔታ ኣስመልክቶ የተደነገገው ከ2010ዓ.ም. የእኩልነት ደንብ ናሕግ ጋር ኣብሮ እንዲካተት እንጠይቃለን፤

**ዓለም አቀፍ ፍትህ፡**

- ከፍተኛ ብዝበዛን ለማስቆም የሚሰራ፤ ኢ-ፍትሃዊ እና ህገ-ወጥ ጦርነቶች ጋር የብሪታንያ መንግሥት ተሳትፎውን እንዲያቆም፤ በተለይ ደገሞ በውጭ አገር የሚገኙ የእንግሊዝ ኩባንያዎች ጭቆናና፡ ኢሰብኣዊ ልምዶች ማዘውተር እንዲያቆሙ እንጠይቃለን፤
- በሰብአዊ መብቶች እና በሰብአዊ ሕግጋቶች በ1951 ጀኔቫ ኮንቨንሺን፡ እንደተጠቀሰው፡ የእንግሊዝ መንግሥት ቃል ኪዳኖችን ሙሉ በሙሉ እንዲፈጽም ፤ ሌሎቸቸ ዓለም አቀፍ ስምምነቶቸቸ እና የተባበሩት መንግስታት አካላት (እንደ UNRWA ያሉ) - በክብር የመኖር መብትን የሚያረጋግጥ እና ደህንነት ፣ ጥገኝነት የመጠየቅ መብት እና ለስደተኞች ወደ ኣገኣራቸው የመመለስ መብት እንዲጠበቅ እንጠይቃለን፤
- ጨቋኞችን የማይደግፍ ወይም የማይረዳ የውጭ ፖሊሲ እንዲኖርና የቅኝ ገዥ እና ጠብ-አጫሪ አገዛዞች ጋር ማበር የእንግሊዝ መንግሥት እንዲያቆም እንጠይቃለን፣
- የእንግሊዝ መንግስት ፍትሃዊ ዓለም አቀፍ የስደት እና የስደተኞች ፖሊሲ ኖሮት፣ የስደተኞች ነጻ ውጭ የመላክ ልምድን እንዲተገብር። የፍልሰት ቁጥጥር ወደግል ኣትራፊ ኩባንያዎች መስጠትና እና ከደካማ የሰብ አዊ መብት ኣራማጆች ፡ እንዲሁም የመመዝገብና፡ የተጠያቂነት ጉድለት ያላቸው ድርጅቶች መተባበር እንዲያቆም እንጠይቃለን፤
- የእንግሊዝ መንግስት አስቸኳይ የአካባቢ (environmental) ፖሊሲ እንዲፈጥር ፡ እነዚህም፡ የወቅቱን ቀውስ የሚመለከቱ እና ጥበቃን የሚያረጋግጡ ሆነው፤ አሁን ያለው የተፈጥሮ አካባቢ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቅና እና በተቻለ መጠን የተጎዱትን የመጠገን አዝማሚያዎች ያላቸው እንዲሆኑ እንጠይቃለን፤

Sign the FIRM Charter

FIRM

**ታሪ ካ ዊ ፍትህ፡**

የቅኝ አገዛዝ ታሪክን እውቅና በመስጠት እና የተውሰዱ ቅርሶች ባለቤትነትን በማስተካከል ብሪታንያ በታሪካዊ ድርጊቷ በሃላፊነት እንድትጠየቅ እናሳስባለን፤

- ለታሪካዊ የብዝበዛ እና የቅኝ ግዛት አመጽ ፣ ካሳዎቸን እና ሌሎች ንብረት የመመለሻ መንገዶችን ኣስተግብሮ ይቅርታ መጠየቅ፤
  በቅኝ አገዛዝ እና በፀረ-ቅኝ አገዛዝ እንቅስቃሴዎች ላይ ፣ ባለፈው እና ዛሬ ፣ በአውደ- ጽሑፋዊ እና በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ዘረኝነትን እና ፍልሰትን የሚያስተምሩ የህዝብ ትምህርት ፕሮግራሞች ማዘጋጀት፤

# 3. መልካም ኣቀባበል እንፈልጋለን (እንጠይቃለን)

- ስደተኞች ፣ ከሚመጡባቸው ማህበረሰቦች ፍላጎት የሚመሳሰል፡ በመልካም አቀባበል ፣ በአብሮነት እና በፀረ ዘረኝነት መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ ብሔራዊ የመደመር ስትራቴጂ የሚወክል እንዲሆን እንፈልጋለን። ይህ ስትራቴጂ እያንዳንዱን ሰው በማህበረሰቡ ውስጥ የተዋቀረ ሁለንተናዊ በቂ ልምድ ያካተት፡ክብር እና መከባበር ኣሟልቶ የሚደግፍ መሆን አለበት፤
- በሀሰተኛ ዜና (fake news) እና በስደተኞች እና በነጭ ያልግሆኑ (BAME) ማህበረሰቦቸች ላይ የጥላቻ ንግግርን የመከላከል አቅም ያለው ገለልተኛ የሚዲያ ቁጥጥር አካል እንዲኖር እንጠይቃለን፤
- የመንግስት የሰፈራ ፕሮግራሞች እንዲስፋፉ እና እንዲራዘሙ እንጠይቃለን፤

# 4. ውጤት እንፈልጋለን (እንጠ ይቃለን)

**የ FIRM ቻርተር ፈራሚዎቾ እንደመሆናችን መጠን ለሚከተሉት የሥራ መርሆዎች እና ዘዴዎች ለማስተግበር ቃል እንገባለን፤ በመርህ ላይ የተመሠረቱ ፣ በስፋት የማደግ ፍላጎት ያላቸው እና በውጤት ስኬታማ ለሆኑት ዘመቻዎች፡ ድጋፍና አስተዋፅዖ እናደርጋለን እና እናመቻቻለን፤**

- በስደተኛ፤ በጥቁር፤ በአናሳ የጎሳ ማህበረሰቦች (ethnic minority communities ) እና ተወካይ አካላት፡ የሚመራ ድርጅቶች ፡ እንዲፈጠሩ እንቅስቃሴ እናደርጋለን፡
- ከግለሰቦች ጋር የሚሰሩና ሁሉንም የሚያካትቱ ንቅናቄ እና ቡድኖችን በእኩልነት መሠረት ወደ ከፍተኛ መግባባት የሚገነባ የዓላማ ክብር እና አንድነት ያላቸው እንዲሆን እንረዳለን፤
- ክልላዊ ፣ ብሔራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ህብረቶችን በማዛመድ ከስደተኞች እና ከስደተኞች ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር፣ ፀረ-ዘረኝነቾ ቡድኖች እና ሌሎች ተራማጅ ኃይሎች እንገነባለን፤ እኩል ሚና የሚጫወቱ ፡ አካባቢያዊ የድርጊት ቡድኖችን ለማቋቋም እንቅስቃሴ እናረጋለን። በዚህ ዘመቻ ተነሳሽነት፡ የድርጊት መርሃ ግብርን ፣ ሥልጠናን ፣ መሰረታዊ ቡድኖች በማደራጀት፡ ተገቢውን የኣካባቢ ሃብቶች ተደራሽነታቸው በማረጋገጥ ረገድ ትልቀ ተራ እንጫወታለን፤
- በዚህ ዘርፍ ውስጥ በህብት ላይ የሚደርሰውን ጎጂ ውድድር ለማቆም እንሰራለን ፣ የጋራ እና የተባበሩ የአሠራር መንገዶችን በማጎልበት ፣ በዚህ ሰነድ (ቻርተር) ውስጥ የተዘረዘሩትን መርሆዎች ፡ በተግባር እንዲውሉ እንሰራለን።

Sign the FIRM Charter

FIRM

# Sign the FIRM Charter

Contact us: info@firmcharter.org.uk
Copyright © 2020

The Fair Immigration Reform Movement Charter platform is powered by Migrant Organise Ltd.